**የግረንፈል ታወር የወደፊቱ እጣ ፈንታ**
ከግንቦት እስከ ሓምሌ 2021 በተካሄዱ ስብሰባዎች የተሰጡ መረጃዎች



**ይህ በራሪ ጽሁፍ ምንድን ነው?**
መንግስት የግሪንፌል ታወር ቦታ ባለቤትነት (ሞግዚትነት) ነው ፡። እኛ ቦታው ደህንነቱ ኣስተማማኝነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ፣ እንዲሁም ስለ ታወር የወደፊቱ እጣ ፈንታን በሚመለት ውሳኔ የማድረግ ሃላፊነት አለብን።

ከግንቦት 2021 ጀምሮ ህንጻው ምን መሆን እንዳለበት እና ምናልባትም የጊዜ ገደቦችን በተመለከተ ስለ ውሳኔ አሰጣጥ መረጃ እናጋራዎታለን። ይህ በራሪ ጽሑፍ ማጠቃልያ ይታቀርባል እናም የእርስዎ ጥያቄዎች እና ስጋቶችን በሚመለክት እኛን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ወይም በወደፊቱ ስለሚደረጉ ነገሮች ያብራራል ።

ይህ ስስ ጉዳይ መሆኑን እንገነዘባለን ፡፡ እንዲሁም ከግንቦት እስከ ሐምሌ ካቀድናቸው ስብሰባዎች ባተጨማሪ እርስዎን በሚስማማ በማንኛውም መንገድ እርስዎን ለመገናኘት እና ከእርስዎ ጋር ለመነጋገር ዝግጁ ነን ፡፡ እባክዎ ይገናኙን።

**የመታሰቢያ ኮሚሽን ሚና ምንድነው?**
መንግስት በአደጋው ህይወታቸውን ያጡ ወገኖችን ለማክበር ተገቢውን መታሰቢያ ለመስራት የአከባቢውን ማህበረሰብ ለመደገፍ ቁርጠኛ ነው ፡፡ የግሪንፌል ታወር የመታሰቢያ ኮሚሽን በሟች የቤተሰብ አባላት ፣ በሕይወት የተረፉ አንዲሁም በአካባቢው ነዋሪዎች ኗሪዎች የቆመ ነው። መታሰቢያ ለማድረግ በማህበረሰብ የሚመራ ራዕይን እያከናወኑ ሲሆን ስራቸውም በማደግ ላይ ይገኛል ፡፡ የመታሰቢያ ኮሚሽኑ ህንጽዳውን በሚመለከት ምን እንደሚከሰት የመወሰን ሃላፊነት የለውም ፡፡

**ለምንድነው አሁን ስለዚህ ጉዳይ እየተናገርን ያለነው?**
የግንቡ (ታወር) ሁኔታን በሚመለከት ከመዋቅር መሐንዲሶች የተሰጡ ጠቃሚ ምክሮችን በመከተል፣ ደህንነትን ለማስጠበቅ ግንቡን በጥንቃቄ ማፍረስ ካለብን እና ከሆነም መቼ መሆን እንዳለበት በዚህ በጋ ማሰብ ኣለብን ፡፡

ይህ የሆነው በሚቀጥለው ጿደይ በህንጻው ውስጥ የሚከናወኑትን የደህንነት ስራዎች ከተጠናቀቁ በኋላ ምን እንደሚሆን ማቀድ እንድንችል ነው ፡፡ እነዚህ የደኅንነት ስራዎች ቀደም ሲል በህንጻው ውስጥ የተገጠሙት 4,500 መደገፊያዎች ለመደጎም አዳዲስ ድጋፎችን (የአሉሚኒየም ወይም የብረት ድጋፎችን) መጨመርን ያጠቃልላል ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ብዙዎቹ ከእሳቱ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ተገጥመዋልል ፡፡

እነዚህ የደህንነት ስራዎች ከተጠናቀቁ በኋላ ህንጻውን በጥንቃቄ ማፍረስ እንድንቀጥል መሐንዲሶች መክረዋል ፡፡ ይህ ማለት አሁን ይህንን ምክር ከግምት ማስገባት አለብን ማለት ነው ፡፡
ይህንን ምክር እርስዎን ማጋራት እና ከግንቦት እስከ ሐምሌ የሚካሄዱት ስብሰባዎች ዓላማ የሆነውን በአንድምታው ዙርያ መወያየት እንፈልጋለን ፡፡

ማንኛውንም ውሳኔ ተግባራዊ ማድረግ ከመጀመራችን በፊት ቢያንስ አንድ ዓመት ያልፋል ፣ ይህም ማለት ከአምስተኛው ዓመት በፊት በህንጻው ምንም ለውጥ አይኖርም ማለት ነው ፡፡

**ህንጻው የተረጋጋ ነው ወይ?**
መሐንዲሶች የግሬንፌል ታወር (ህንጻ) የተረጋጋ መሆኑን አረጋግጠዋል ፡፡ ህንጻውን በተቻለ መጠን ሙሉ በሙሉ ለመጠበቅ ከእሳቱ በኋሏ ወዲያውኑ መደገፊያዎች ተቀምጧል፣ ሌሎች የደህንነት እርምጃዎችም ተወስዷል ። ይህ የፖሊስ ምርመራዎችን እና ወደ ታወር የሚደረጉ ጉብኝቶችን ለማመቻቸት ደህንነቱ የተጠበቀ መዳረሻ እንዲኖር አስችሏል ፡፡
የህንሳው የቅርብ ክትትል እና ጥገና ቀጥሏል። የታወሩ መረጋጋትን ለመገምገም የኣውቶማቲክ ስርዓት ተገጥሟል እንዲሁም በየቀኑየ 24 ሰዓት በየፎቁ መደበኛ ፍተሻ በየሚደርጉ መዋቅራዊ የምህንድስና ባለሙያዎች የተሟላ ነው ፡፡

ብህንጻው ዙርያ የተገጠሙ መደግፊያችን ጨምሮ ፣ የህንጻውን መረጋጋት ለመጠበቅ እስካሁ የመደገፍያና የጠርዝ ስራዎችበሙሉ ተጠናቋል ። ይህ ማለት ሰዎች በአቅራቢያው መኖር ፣ መማር እና መስራትን መቀጠል ይችላሉ ማለት ነው ፡፡

ሆኖም ግን ፤ቀጣይነት ያለው የደህንነት ስራዎች አካል በመሆን ተጨማሪ መሞከሪያ እንኳን ቢሆን ፣ በእሳቱ ምክንያት በህንጻው ላይ የደረሰው ጉዳት - የህንፃው ሁኔታ እየተባባሰ ይቀጥላል ማለት ነው ፡፡

**የህንጻው ሁኔታን በሚመለከት የምህንድስና ምክር ምን ይላል?**
እሳቱ በወለሉ ንጣፎች በታች ያለው ኮንክሪት እና በአንዳንድ ግድግዳዎች እና አምዶች ላይ ኮንክሪት ላይ ጉዳት ኣድርሷል ፡፡ ይህ የመዋቅሩ ኮንክሪት ከመዋቅሩ እንዲላቀቅ ኣድርጓል ወይም ሊያደርግ ይችላል ፡፡ ይህ ዓይነቱ ጉዳት በኢንጂነሮች ‹እስፓሊንግ› በመባል የሚታወቅ ሲሆን አንዳንድ ቦታዎችን መጠገን የማይችሉ እንዲሆኑ ኣድርጓል ፡፡

የሕንፃው ሁኔታ እንዲሁ ለንጥረ ነገሮች መጋለጥ እና ተለዋጭ ማቀዝቀዝ እና ማቅለጥ በከረምት እና በበጋ ወቅት እንዲነካ ያደርጋል ፡፡ ከጊዜ በኋላ ይህ የህንፃውን ተጨማሪ መበላሸት ሊያስከትል ይችላል ፡፡

በዚህ ምክንያት ፣ እነዚህ የደህንነት ስራዎች በሚቀጥለው ጿደይ ከተጠናቀቁ በኋላ ህንጻውን በጥንቃቄ ማፍረስ እንድንቀጥል መሐንዲሶች መክረዋል ፡፡

እንዲሁም የተቀበልነውን የምህንድስና ምክርን በገለልተኛ መሐንዲስ አማካይነት የአቻ ግምገማ አድርገናል ፡፡ ያሉንን በትክክል እንዲያዩ ምክሮቻቸውን ከሌሎች መሐንዲሶቻችን ጎን ለጎን እናወጣለን ።

**በወደፊቱ የግንባታው እጣ ፈንታ ውሳኔ ላይ ምን ሌላ ተጽዕኖ ይኖራል?**
በ2018፤ በሚከተሉት መርሆች በቁርጠኝነት ይዘናል:

- ወደ መታሰቢያው በሚሄዱ በእያንዳንዱ እርምጃ ከማህበረሰቡ በተለይም በሐዘን ላይ ካሉ ቤተሰቦች ኣስተያት መስማት
- በአቅራቢያ የለሚኖሩ ፣ የሚሰሩ እና የሚማሩ ሰዎች ጤንነት እና ደህንነት ቅድሚያ መስጠት
- ውሳኔው በማስረጃ የተመሠረተ እና በባለሙያዎች የተላለፈ መሆኑን ማረጋገጥ
- በግሬንፌል ታወር አጣሪ ወይም በፖሊስ በኩል ለፍትህ በሚደረግ ሂደት ጣልቃ አለመግባት ፡፡

በግንቦት ወር መጨረሻ በእነዚህ መርሆዎች ዙርያ የተቀበልነውን ምክር ይፋ እናወጣለን ፣ ይሄም ምን መሆን እንዳለበት ለሚያሳውቅ ውሳኔ ግብኣት ይሆናል፡፡ ይህ በበጋ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ምክሩን ከግምት ውስጥ ለማስገባት ፤ በእሱ ላይ ያሚኖርዎት አስተያየት ለማቅረብ እና ማናቸውንም ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ለማንሳት እድል እንዲያገኙ ነው።

**ህንጻው ለቀጣይ የግሬንፌል ታወር ኣጣሪ ወይም ለፖሊስ ምርመራ አስፈላጊ ነውን?**
ውሳኔዎች በስራቸው ላይ ጣልቃ የማይገቡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ መንግስት ከሜትሮፖሊታን ፖሊስ ፣ ከኮሮነር እና ከግሬንፌል ታወር አጣሪ ጋር መደበኛ ግንኙነት ያደርጋል ። ከህንጻው የሚፈልጉትን ሁሉም ማስረጃ እንዳላቸው አረጋግጠውልናል ።

**የወደፊቱ መታሰቢያን በሚመለከት ምን እየሆነ ነው?**
መንግስት በአደጋው ህይወታቸውን ያጡ ወገኖችን ለማክበር ተገቢውን መታሰቢያ ለመስራት የአከባቢውን ማህበረሰብ ለመደገፍ ቁርጠኛ ነው ። የተወሰኑ የህንጻው ታማው ክፍሎች እንደ መታሰቢያው አካል ኢንዲሆን ከፈለጉ ሊቆዩ እንደሚችሉ መንግስት ለመታሰቢያው ኮሚሽን ቃል ገብቷል። ለተጨማሪ መረጃ እባክዎ የሚከተለውን ይጎብኙ: [www.grenfelltowermemorial.co.uk](http://www.grenfelltowermemorial.co.uk)

**ቀጥሎ ምን ይሆናል?**
ማንኛውንም ውሳኔ ተግባራዊ ማድረግ ከመጀመራችን በፊት ቢያንስ ኣንድ አመት ይቆያል ፡፣
በ 2022 አምስተኛው ዓመትከምከበሩ በፊር ብህንጻው የሚታይ ለውጥ ኣይኖርም ።

- **እስካሁን ድረስ**፡ ከበጋ 2000 ዓ.ም. ጀምሮ በህንጻው የደህንነት ስራዎች እየተሰሩ ናቸው።

- ***ግንቦት - ሓምለ 2021፡***

  - ኤም ኤች ሲ ኤል ጂ እና መዋቅራዊ መሃንድሶቻችን ስለ ተቀበልናቸው ምክሮች ያናግርዎታል። ይህ የሚካሄደወ በቤተሰብ ድጋው መረብ ስብሰባዎች ፣ በኦንላይን በኣንድ ለኣንድ ውይይቶች ኣማካይነት ነው ።

  - ገለልተኛ የተሳትፎ ድርጅት ፣ ካይዘን እስከ ሓ መጨረሻ ድረስ አስተያየቶችዎን መቀበሉን ይቀጥላል (በዚህ በራሪ ወረቀት መጨረሻ ላይ የሚገኙትን የግንኙነት ዝርዝር ይመልከቱ)።

- ***በግንቦት ወር መጨረሻ፡*** በነዚህ መርሆዎች ዙርያ የተቀበልነውን ምክር ይፋ እናወጣለን ፣ ይሄም የምህንድስና ምክርን ጨምሮ በህንጻው ምን ምደረግ እንዳለበት የሚያሳውቅ ውሳኔ ኣክካል ይሆናል። ይህ እሱን ከግምት ውስጥ ለማስገባት እና ማንኛውንም ጥያቄ ለመጠየቅ ጊዜ ለመስጠት ነው ።

- በሐምሌ ወር መጨረሻ፡ ይፋ በወጣው መረጃ ላይ እስከ ሐምሌ መጨረሻ ድረስ ማንኛውንም አስተያየት እንቀበላለን ። የካይዘን ህንጻን በሚመለከት ብካይዘ የሚሰበሰቡ እይታዎች በዛን ጊዜ ይጠናቀቃሉ ።

- **በ 2021 ክረምት መጨረሻ ላይ፡** በነሐሴ ወይም በመስከረም ወር ሁሉንም እይታዎች ውክልናዎችን ክሰማን በኋላ ውሳኔውን መወሰን እንጠብቃለን ፡፣

- **2021 - 2022፡** ሚቀጥለው ዓመት ታወሩን ማፍረስ መጅመርን የሚለው የመሃንዲሶች ምክረ ሃሳብ መከተል ከተወሰነ ፣ ማፍረሱን የሚያካሄድ ልዩ ኩባንያ ይመደባል። ግንቡን ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ ለማፍረስ ዝርዝራዊ እቅድ ያዘጋጃሉ። (ይህ የጥገና እና ደህንነት ስራዎችን ከሚያከናውን የአሁኑ ኮንትራክተር በተጨማሪ ይሆናል፡፣ ይህንን እንዴት በተሻለ መንገድ እንደምንቀርበው ለማሳወቅ በሐዘን ላይ ያሉ ፣ በሕይወት የተረፉ እና የነዋሪዎችን አስተያየት እንደገና እንፈልጋለን ።

**ይፋ እያደረግነው ባለ መረጃ ዙርያ የርስዎ ጥያቄዎች እና ስጋቶችን መስማት እንፈልጋለን፣ በዛው ከርስዎ ለመወያየትም ዝህጁ ነን።**

**እኛን የሚያነጋገሩበት በርካታ መንገዶች ኣሉ፡**

- ለሌላ የግል የቤተሰብ የድጋፍ መረብ ስብብሰባ ቀጠሮ መያዝ ወይም በሚከተለው የኦንላይ ገለጻ ከኛ ጋር ማድረግ ይችላሉ፡ [Grenfell2021.eventbrite.com](http://Grenfell2021.eventbrite.com)

- ወደ **GrenfellTowerSite@communities.gov.uk** ኢመይል በመላክ ወይም **በ 0303 444 0011** በመደወል የኣንድ ለኣንድ ውይይት ከኛ ጋር ያዘጋጁ ።

- ወደ መደበኛው ያለ ቀጠሮ የሚካሄዱ የኦንላይን ስብሰባዎቭ ይገኙ። አርብ ዓርብ የ ኤም ኤች ሲ ኤል ጂ የማህበረሰብ የተሳትፎ ቡድን በክሌመንት ጀምስ ቸንተርል ( ብፍሮን ጋርደን ስቱዲዮ) በ 95 Sirdar Road, London W11 4EQ ይኖራል። **በግንቦት 21 እና በግንቦት 28 ፣ 4 እና 5 ሰነ፣ 2 ፣ 9 ፣ 16 እና 23 ሓምሌ** እዛው ይኖራሉ። ቀጠሮ ለማያዝ እባክዎ ኢሜይል ይላኩልን።

- ካይዘን ፣ ገለልተኛው የተሳትፎ ማህበር፣ ህንጻውን የሚመልከቱ እይታዎችን በመሰብሰብ እያገዘን ነው። **በgrenfelltower@kaizen.org.uk 020 7082 5505 ማናገር( ወይም ወደ 07984 434855** የጽሁፍ መል እክት በመላክ ሊያገኙን ወይም ደሞ የሚከተለውን በምንብኘት ሊያገኙን ይችላሉ፡ www.surveymonkey.com/r/GrenfellTower

***ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት***

- በኢሜል ለሚሰጡ መረጃዎች በዚህ ይመዝገቡ www.gov.uk/grenfell-community-updates
- በዚያው ዌብ ሊንክ ፣ ከመዋቅራዊ መሃንዲሶች ጨምሮ የተቀበልነው ምክር - ከህ ወር መጨረሻ ጀምሮ በሙሉ ኡገኛሉ።

**የጤና እና የደህንነት ድጋፍ**
እርዳታ አለ ፣ ከፈለጉ እባክዎ በዚሑ ይገናኙ ፡፡

የሆነ ሰው ለማነጋገር ፣ ኔ**ወደ NHS ጤናና እና ደህነንት አገለግሎት በ020 8637 6279 በመወል የናጋሩ።** ከሰኞ እስከ አርብ ፣ ከጧቱ 8 ሰዓት እስከ ምሽቱ 8 ሰዓት ክፍት ናቸው።

ማነጋገር ከፈለጉ ትጉህ የሆኑ የድጋፍ ሰራተኞች ለማገዝ ዝግጁ ናቸው።
ሊያገኙት ስለሚፈለጉት ድጋፍ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ እባክዎ የሚከተለውን ይጎብኙ፡ bit.ly/NorthKenNHS

**ይህን ስላነበቡ እናመስግንዎታለን**